# አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ

/፲፱፻፩ – ፲፱፻፹/

## ከቤተ ክህነት እስከ ማስታወቂያ ሚኒስቴር

በተስፋዬ ሸብሩ



«ለኢትዮጵያ ታሪኳ
ነው መልኳ»

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ የልደት በዓላቸውን በየዓመቱ ሐምሌ ፲፮ ቀን ያከብሩ በነበረት ጊዜ የሚያስቀድሱት በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጽር ግቢ ውስጥ በምትገኘው በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ነበር::

ንጉሡ ሥርዓተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ከመመለሳቸው በፊት፣ አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ የተባሉ ሊቅ ይህንኑ ታሪካዊ ቀን በማስመልከት ንግግር ያደርጋሉ::

እኝህ ሊቅ ሃያ አንድ ዓመት ሙሉ ያለማቋረጥ በንጉሡ ፊት ንግግር አድርገዋል:: በዚህም በንጉሡ እና በቅርብ ባለሟሎቻቸው ዘንድ ሊታወቁ ችለዋል::

ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም /በ፲፮ኛው ዓመት ንግግራቸው/ ግን ከሌላው ጊዜ ሁሉ ለአፈ ሊቅ የተለየ ቀን ነበር:: በዕለቱ ከዐዜ ዘርዐ ያዕቆብ የተያያዘውን የተዋሕዶ ሃይማኖት ታሪክ ጠቅሰው በንጉሡ ፊት ሰፋ ያለ ንግግር አደረጉ:: በተመስጦ ሲከታተሏቸው የነበሩት ንጉሥ አንድ ነገር በልባቸው ያስቡና ወደ ቤተ መንግሥታቸው ይመለሳሉ::

ሊቁም አገር አማን ብለው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ:: አንድ ቀን ለካስ ተፈልገው ኖሮ ያን ሊቅ ጥሩ ይባልና ከቤተ መንግሥት እቤታቸው ሰው ተልኮ እንዲጠሩ ይደረጋል:: ሊቁም ከዋናው የእልፍኝ አስከልካይ ከጄኔራል አሰፋ ደምሴ ዘንድ ይቀርባሉ::

«ንጉሡ ሊያነጋግሩዎት ይፈልጋሉ» ይሏቸዋል ጄኔራሉ:: ንጉሡም ከእልፍኛቸው ሰገነት ላይ ሆነው ግራና ቀኝ ይንጎራደዳሉ:: አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ልዑላትና ልዑላን ሌሎችም መኳንንት የሰገነቱን መሐል ክፍት አድርገው ግራና ቀኝ ቆመዋል:: አፈ ሊቅ በዋናው የእልፍኝ አስከልካይ አማካይነት ንጉሡ ፊት ሲቀርቡ ዝቅ ብለው እጅ ነሱ::

አፈሊቅ በጊዜው የሆነውን ሲያስታውሱ «ነገሩ የሆነው ሳይታሰብ ነበር እና ጎንበስ ብዬ እጅ ነሥቼ ቀና ለማለት እስከ መቸገር ደርሼ ነበር:: ከድንጋጤዬ የተነሳ እንደምንም ቀና ብዬ ንጉሡን አየኋቸው:: እጃቸውን ወደ ኋላ አድርገው ይንጎራደዳሉ:: ግርማ ሞገሳቸው ያስፈራል፣ ያስደነግጣል:: ግራ ቀኙን በዐይኔ ሳማትር ደግሞ ከዚያ ሁሉ ታላላቅ





ባለ ሥልጣን መሐል ካባ የለበስኩትና የጠመጠምኩት እኔ ብቻ ነበርኩ:: ጃንሆይ ወዲያውኑ ሊቁን መጠየቅ ጀመሩ::

*ጃንሆይ፦* በየጊዜው የምታደርጋቸው ታሪካዊ ንግግሮች ሁሉ አንድ ከፍ ያለ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ይመስለናል:: ለመሆኑ ልታሳትመው ታስባለህ?

*አፈሊቅ፦* ግርማዊ ሆይ ማሰቤስ አልቀረም:: የማሳተሚያው አቅም ስለሌለኝ ብቻ ነው::

*ጃንሆይ፦* አንተ አዘጋጅተህ አቅርበው እንጂ የማሳተሚያውን ዋጋ እኛ እንረዳሃለን:: /ከዚህ በኋላ ነው አፈ ሊቅ «ለኢትዮጵያ ታሪኳ ነው መልኳ» የተሰኘውን ድርሰታቸውን ማዘጋጀት የጀመሩት/

*ጃንሆይ፦* ለመሆኑ ይህንን ሁሉ ዕውቀት የገበየኸው የት ነው?

*አፈ ሊቅ፦* ለቅኔ ትምህርት ወደ ዝቋላ ሄጄለሁ እንጂ በሙሉ የተማርኩት እዚሁ ነው:: በተለይ የሐዲስን ትርጓሜ ከሊቁ ቀጸላ ዘንድ በምማርበት ጊዜ /በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ግርማዊነትዎ አልጋ ወራሽ ሳሉ/ ለእኔና ለሌሎች አራት ደቀ መዛሙርት በወር ቀለብ ቆርጠውልን የሁሉንም ተማሪዎች ደመወዝ እኔ እየተቀበልኩ ነው የተማርኩት::

*ጃንሆይ፦* ጊዜው ምንም ቢቆይ ትዝ ይለናል:: ለመሆኑ ስለ እመቤታችንና ስለ ዮሴፍ አንድ ላይ መኖር የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል መርምረኸዋል?

*አፈ ሊቅ፦* ዕድሜ ለግርማዊነትዎ የዘመኑን ትምህርት /በተለይ እንግሊዝኛን/ በመጠኑም ቢሆን ተከታትየዋለሁ:: በዚህ ምክንያት የአማርኛውንና የእንግሊዝኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተያየትና ለማገናዘብ አልተቸገርኩም:: ግርማዊ ሆይ የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ እመቤታችንን ለዮሴፍ ሚስቱ ሲል፣ ግእዙ ፍህርቱ፣ አማርኛው እጮኛው ይላል::

*ጃንሆይ፦* ታዲያ የትኛው ነው ትክክል ትላለህ?

*አፈ ሊቅ፦* የአማርኛውና የግእዙ ነው ትክክሉ::

*ጃንሆይ፦* እነሱ እኮ «ኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት ወልደ ዘበኩራ...» /ልጅ እስከ ወለደች ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም/ ያለውን ይዘው ነው::

*አፈ ሊቅ:-* ይህማ «እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ የለውም:: ለዚህ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ዮሐንስ አፈወርቅ «ኢወለደት ወልደ ሚልኮል እስከ አመ ሞተት» ብሏል:: «እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አል ወለደችም::» ከሞተች በኋላ ወለደች ይባላልን?» ግርማዊ ሆይ?

*ጃንሆይ:-* ዮሐንስ አፈወርቅንና ቄርሎስን አዋልድ ናቸው በማለት ምስክርነታቸውን አይቀበሉም እኮ...!

*አፈ ሊቅ:-* አዋልድ ማለት ልጆች፣ ሐዲሳት ማለት አባቶች፣ ብሉያት ነቢያት ማለት አያቶች ማለት ነው:: ከነተረቱ «አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው እንዲሉ እነዚህ መንፈሳውያን አዋልድ መጻሕፍት የተውጣጡት ከብሉያት፣ ከነቢያትና ከሐዲሳት ነው እንጂ እንደ ሥጋዊ መጻሕፍት ያለመንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት በሥጋዊ የተደረሱ አይደሉም::

*ጃንሆይ:-* ፈገግ አሉና ረዘም ያለ ጊዜ ወስደው ጥያቄ እና መልሱን በስፋት ቀጠሉ:: ወዲያው የእልፍኝ አስከልካዩ አፈሊቅን ጠጋ ብለው «ንጉሡ ደክሟቸዋል:: ይበቃችኋል:: ሽልማት ታዞልዎታል» ይላቸውና ወደ ውስጥ ይገባሉ:: የዘውድ ምልክት ያለበት ልዩ ካባ ከጥንድ ድርብ እና ከሙሉ ክብሩ ጋር ለብሰው ንጉሡን እጅ ነስተው ወደ ቤታቸው ያመራሉ:: ለሚቀጥለው ዓመት የሚያደርጉትን ንግግር በአእምሯቸው እያሰላሰሉ::

አፈ ሊቅ እንዳጫወቱኝ ይላሉ ልጃቸው አቶ ንጉሤ አክሊሉ ጃን ሆይ ግእዝ በሚገባ ያውቃሉ:: ትርጉሙን ብቻ ሳይሆን ግእዙን በሚገባ ይናገሩታል:: «ኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት... ያለውን ይዘው ነው» ሲሉኝ... ግእዝ አዋቂነታቸውን ይበልጥ ላረጋግጥ ችያለሁ ብለዋል አፈ ሊቅ::

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገ/ኪሮስ ከወ/ሮ እንተ ማርያም ሠረቀ ብርሃንና ከመሪጌታ ገብረ ኪሮስ ኃይለ ገብርኤል መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ዋሻ ማርያም እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ተወለዱ::





በአራት ዓመታቸው በአያታቸው ቤት ትምህርት /ፊደል መቁጠር/ ይጀምሩና በተለያዩ ችግሮች የተነሣ የጀመሩትን የፊደል ትምህርት ያቋርጣሉ:: ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ በ፲፱፻፲ ዓ.ም ያቋረጡትን ትምህርት ጀምረው ንባብና ዳዊት በአንድ ዓመት ውስጥ ደግመው በማጠናቀቃቸው ድግስ ተደግሶ ለወላጆቻቸውና ለአያቶቻቸው የምሥራች ተብሏል::

በ፲፱፻፲፩ ዓ.ም ሚያዝያ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በጊዜው ከነበሩት ሊቀ ጳጳስ ከአቡነ ማቴዎስ ማዕርገ ዲቁና ተቀብለዋል:: ከዚህ በኋላ የዜማ ትምህርት ለመቀጸል እንዲችሉ አባታቸው አዲስ አበባ ጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ደብር ያስተምሩ ከነበሩት ከሊቀ ጠበብት ደስታ ተገኝ ዘንድ ልከዋቸው ተምረዋል:: በሁለት ዓመት ከስድስት ወር የቆይታ ጊዜያቸው ጾመ ድጓና ምዕራፍ ካጠኑ በኋላ ወደ ዝቋላ ገዳም ተጉዘው ወንበር ማርያም ከተባለች ደብር ብሉይና ቅኔ ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ደስታ ቅኔ ቀጽለዋል:: በዚሁ ገዳም ቅኔ ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ኮከብ ዘንድ ቅኔ እስከ ዘይእዜ ያለውን ጉዳና ተምረዋል:: በመጨረሻም የሐዲስና ዜማ አቋቋም መምህር ከነበሩት ከሊቄ ቀጸላ ወልደ መድኅን ቅኔውን ከነግሡ እርባታ ካስፋፉ በኋላ ለመቀኘት ሲበቁ በጉለሌ ሩፋኤል ደብር እንዲቀኙ ተፈቅዶላቸው ለደብሩ አለቃ ለአለቃ ሠርጹ ኃይሌ ደብዳቤ ተጽፎ ከዝቋላ ገዳም መጥተው ተቀኝተዋል::

በ፲፱፻፲፬ ዓ.ም ወደ ዝቋላ ገዳም በመመለስ ቅኔውን በማስፋፋት ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፲፭ ዓ.ም መምህራቸውን ሊቄ ቀጸላን ተከትለው ወደ አዲስ አበባ መጡ:: ሊቄ ቀጸላ ግቢ ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት እንዲያገለግሉ ሲመደቡ እርሳቸውም በዚህችው ቤተ ክርስቲያን የቅኔውን አገባብ ቀጸሉ:: ከዚህ በኋላ የታወቁት መምህር ወልደ ጊዮርጊስ እንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ ያስተምሩ ነበር:: አክሊሉ ገ/ኪሮስም ከኒሁ መምህር የግብረ ሐዋርያትን ትርጓሜ መማር ጀመሩ:: ከዚያም አባታቸው በቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ብሉይና ቅኔ ያስተምሩ ከነበሩት ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ ዘንድ ቅኔያቸውን እንዲያስፋፉ የብሉያትንም ታሪክ እንዲሰሙ ልከዋቸዋል::

የዳዊትን፣ የዳንኤልን፣ የኢሳይያስን ትርጓሜ ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ ወልደ አማኑኤል አጥንተው የኦሪትን ትርጓሜ እንደ ጀመሩ አባታቸው መምህር ገብረ ኢየሱስ በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ኅዳር ፲፬ ቀን በማረፋታቸው መምህር ገብረ ኢየሱስ ... ቸው የትምህርት ትጋታቸው በብርቱ ኀዘን ታወከ:: ኀዘኑ ቢበረታባቸውም አባ እንግዳ የሚባሉ መምህር በዚያው በቀጨኔ መድኃኔዓለም ቅኔ ያስተምሩ ስለ ነበር ቅኔውን እያስፋፉ ከቆዩ በኋላ መምህራቸው ለማስተማር የበቁ ናቸው በማለት እንዲያስተምሩ ፈቀዱላቸው::

አፈሊቅ አክሊሉ በነበራቸው የመማር የማወቅ ፍላጎት የተነሣ ወደ ተለያዩ መምህራን በመሄድ ዕውቀታቸውን ያስፋፉ ነበር:: በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ስመ ጥሩው አለቃ ለማ ኃይሉ የቀጨኔ መድኃኔዓለምን ደብር ዕልቅና ተሹመው በመጡ ጊዜ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ የሐዲስን ትርጓሜ ከሳቸው መማር ጀመሩ:: አለቃ ለማም የተዋሕዶ ሃይማኖት ዋና አብነትና ሊቅ እንደ መሆናቸው መጠን ብዙ ምሥጢር አስጠንተዋቸዋል:: አለቃ ለማም የአፈ ሊቅ የቀለም አያያዝ ችሎታ ስላስደነቃቸው «የዚህን ልጅ ራትና ምሳውን ሳልችል የቀረሁ እንደ ሆነ እኔ ለማ አይደለሁም» እያሉ ለባለቤታቸው ይነግሯቸው ነበር:: በኋላ ላይ ግን ለአራት ተማሪዎች ከመንግሥት ቀለብ ተሰጥቷቸው እንዲማሩ መፈቀዱን ሊቁ ቀጸላ ለአክሊሉ ይነግሯቸዋል:: በዚህ ጊዜ ከቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ወደ ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት መዛወር ግድ ሆነባቸው:: ሊቁ ቀጸላም ቀለም ይገባሃልና አንዱ ቀለብ ለአንተ እንዲሰጥ ፈቅጄልሃለሁ:: ስምህም በጽሕፈት ሚኒስቴር እንዲገባ ተደርጓል ብለው ይነግሯቸዋል:: ስለዚህ ከ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ድረስ ለዘጠኝ ዓመታት የሐዲሳት ትርጓሜን በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ተከታትለዋል::

በመቀጠል ከቀጨኔው የድጓ መምህር ከአለቃ ወልደ ዮሐንስ፣ ከመሪጌታ መርዓዊ ከየኔታ ዘለዓለምና ከአለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ዝማሬ መዋስዕትና አቋቋም፣ ከአባ ገብረ ትንሣኤ የተክሌን ዝማሜ አጥንተዋል:: አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ያስጠኗቸውን ዜማ ደህና አድርገው ስለ ያዙላቸው ዝማሬ መዋስዕቱን አስተምር ብለው ፈቅደውላቸው ነበር::





የሃይማኖት ጥያቄ ለመመለስ እንዲችሉ የሊቅ ትምህርት ለመማር ወደ ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማርያም ዘንድ በመሄድ ትምህርት ጀመሩ:: ከ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ጀምሮ ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ እስከ ዐረፉበት ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ድረስ ለሃያ ሦስት ዓመታት የሃይማኖተ አበው፣ የዮሐንስ አፈወርቅ የቅዱስ ቄርሎስን መጻሕፍት፣ ትርጓሜን አጥንተዋል::

አፈሊቅ አክሊሉ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ከመማር ከማንበብ አልተለዩም ነበር:: ለዚህም «ሊቅ እየተማረና እያስተማረ ይሞታል»፣ «ያነበበ ዕውቀትን ጠገበ»፣ «መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ» የሚሉ ብሂሎችን ዘወትር ይጠቀሙ ነበር::

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ አቶ በትረ ጽድቅ ካሣ በተባሉ መምህር እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲያጠኑ ከተመረጡት የቤተ ክህነት ሊቃውንት መካከል አንዱ በመሆን በላይኛው ቤተ መንግሥት /በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ/ ሲከታተሉ ቆይተው በቅድስት ሥላሴ ት/ቤት አባ ማርቆስ የተባሉ ግብጻዊ የቋንቋ መምህር ተሰጥቷቸው እስከ ፰ኛ ክፍል ድረስ ተምረዋል:: በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም በቤተ ክህነት የድርሰት ክፍል ሥራ በመጀመራቸው የተነሣ በቅድስት ሥላሴ ጀምረውት የነበረውን የቋንቋ ትምህርት አቋርጠው በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በአሜሪካን ኢንስቲትዩት ት/ቤት በመማር የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል::

አፈ ሊቅ አክሊሉ በቤተ ክህነትና በመንግሥት ሥራ ላይ

ከ፲፱፻፴፰-፲፱፻፶፫ ዓ.ም ድረስ ለ፲፭ ዓመታት በጠቅላይ ቤተ ክህነት በድርሰት ክፍል በዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በየበዓሉ የሚወጡትን ድርሰቶችና እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊ ሥርዓትና እምነት የሚቃወም ጽሑፍ ሲወጣ ለዚያ መልስ የሚያዘጋጁ አፈሊቅ አክሊሉ ነበሩ:: ይህም መልስ የሚሰጡበት መጽሔት «መርሐ ምእመናን» በመባል የሚታወቅ ነው::

በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ንዋየ ቅድሳት ሁሉ አዲስ አበባ ላይ ተሰብስበው እንዲቆዩ ተደርጎ በነበረ ጊዜ

«መዘክረ ምግብ መንፈሳዊ» የተባለውን ድርሰት በትእዛዝ አዘጋጅተው ያቀረቡት አፈሊቅ አክሊሉ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪም ዜና ባስልዮስ የተባለ መጽሔት አዘጋጅተው አቅርበዋል:: የሃይማኖት ክርክር በተነሣ ጊዜ በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ጉባኤዎች ተካፋይ ከመሆናቸውም በላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀው ሦስተኛው የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጉባኤም ላይ በመገኘት በወቅቱ ለተነሱ የሃይማኖት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል::

በቤተ ክህነት በማገልገል ላይ እያሉ በግእዙ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኘውን ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያምን በጽሕፈት ሚኒስቴር ትእዛዝ ከግእዝ ወደ አማርኛ ተርጉመው በማቅረብ እስከ አሁን ድረስ እያገለገለ ይገኛል::

አፈ ሊቅ አክሊሉ በነበራቸው ጥልቅ የሥነ ጽሑፍ ችሎታና ዝንባሌ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ከቤተ ክህነት ወደ ማስታወቂያ መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ተዛውረው እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ድረስ ለ፲፫ ዓመታት አገልግለዋል::

በአዲስ ዘመን ጋዜጣና በኢትዮጵያ ሬዲዮ ታሪክ ጠቀስ የሆኑ የሐተታ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ይሠሩ ነበር:: በተጨማሪም በኢትዮጵያ ሬድዮ «አባትህን ጠይቀው ይመልስልሃል» በሚል ርእስ ትምህርታዊ የጥያቄና መልስ ፕሮግራም እያዘጋጁ ያቀርቡ ነበር::

በዚሁ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በሥነ ጽሑፍ ምርመራ አገልግሎት ውስጥ ልዩ ልዩ ድርሰቶችን በማረም ሠርተዋል:: በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ከማስታወቂያ ሚኒስቴር በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በቤታቸው ጽሑፎችን እያዘጋጁ ቆይተዋል:: የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት በሆኑት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትዕዛዝና ፈቃድ በ፲፱፻፸ ዓ.ም እንደ ገና ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተመልሰው በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት እስከ ፲፱፻፸፬ ዓ.ም ድረስ በእርማትና በመጻሕፍት ምርመራ ክፍል አገልግለዋል:: በጠቅላላ ለሃምሳ አንድ ዓመታት በቤተ ክህነትና በመንግሥት ሥራ ያገለገሉ ሲሆን በመጨረሻ የሕይወት ዘመናቸው አካባቢ በሕመም ቢያዙም እንኳ በዜና ቤተ ክርስቲያን፣ በአዲስ





ዘመንና በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች ላይ ስለ ግእዝ ቋንቋና ታሪክ በተደጋጋሚ በመጻፍ፣ ስለ ኢትዮጵያ በዓላትም በሬድዮና በቴሌቪዥን ለሚቀርቡላቸው ቃለ ምልልሶች በቂ መልስ በመስጠት እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ እንደበታቸው መልስ ከመስጠት ሳይገታ ጣታቸው ብዕር ከመጨበጥ ሳይረታ ቆይቷል::

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ይሠሩ በነበረበት ወቅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅ /አንጋፋው ጋዜጠኛ ነጋሽ ገብረ ማርያም/ ለአፈ ሊቅ «ኤዲቶሪያል ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ምን አማርኛ ትርጓሜ እንስጠው?» ሲል ይጠይቃቸዋል:: ሊቁም፣ በሐዲስ ትምህርት፣ አንቀጸ-ትምህርት፣ አንቀጸ-ጾም፣ አንቀጸ-ምጽዋት አንቀጸ-መስዋዕት የሚል መኖሩን ለጋዜጣው ዋና አዘጋጅ በአስረጅነት ከገለጹላቸው በኋላ፣ ርእሰ-አንቀጽ ቢባል የሚስማማ መሆኑን ይገልጹላቸዋል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ርእሰ አንቀጽ የሚለው ጸድቆ እስከ ዛሬም ድረስ እያገለገለ ይገኛል::

በዚሁ መሥሪያ ቤት ይሠሩ በነበሩበት ጊዜ በመንግሥት ትእዛዝ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ ታሪክ እንዲመረምሩ ለተላኩት የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ የጋዜጠኞች ቡድን መሪ በመሆን ግሼን ደብረ ከርቤ ማርያም ቡድኑን በመምራት ሄደው «ጤፉት» ከተባለው መጽሐፍ የመስቀሉን አመጣጥ ታሪክ ከግእዝ ወደ አማርኛና እንግሊዝኛ እንዲተረጎም በማድረግ ታሪኩን በመጽሔት ጽፈው በማቅረብ ከፍተኛ ተግባር ፈጽመዋል::

በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም ከሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ /በኋላ በብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ/ አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ተብለው ተሹመዋል:: ይህም ሹመታቸው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመክሮ የጸደቀ ነው::

አቶ ንጉሤ አክሊሉ የአፈ ሊቅ አክሊሉ ገ/ኪሮስ ልጅ ናቸው:: በአንድ ወቅት የእሑድ ፕሮግራም የሬዲዮ ጋዜጠኛ በነበሩበት ጊዜ ከአባታቸው ጋር ቃለ ምልልስ የማድረግ አጋጣሚ አግኝተው ነበር:: በዚያ ወቅት የነበረውን ሁኔታ ጋዜጠኛ ንጉሤ አክሊሉ እንዲህ ያስታውሱታል::

በወርኃ ግንቦት ጋብቻ ለምን አይፈጸምም? ቤተ ክርስቲያንስ በዚህ ላይ ያላት አቋም ምንድን ነው? የሚለውንና የኅዳር በሽታንና የኅዳር መታጠንን አስመልክተን ለእሑድ ጠዋት የሬዲዮ ፕሮግራም አንድ ዝግጅት እንድናቀርብ እኔና የሥራ ባልደረባዬ እና ጓደኛዬ አዲሱ አበበ /ዛሬ የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጋዜጠኛ/ በአለቃችንና በመምህራ ችን በጋዜጠኛ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ እንታዘዛለን:: «ይሄ የቤተ ክርስቲ ያን ጉዳይ ስለሆነ ንጉሤ ቢሠራው ይሻላል ይላል አዲሱ:: እሱ በደጁ ያላ ለፈ ይመስል...:: መሥራቱንስ ልሥራ ለመሆኑ ማነው ተጠያቂው?» አልኩ:: አፈሊቅ ናቸው አባትህ...» አለኝ አለቃዬ:: «አባቴን ኢንተርቪ ው ሳደርግ ሰው ጉድ አይልም?» በማለት መከራከር ጀመርኩ:: በብዙ ክርክር ሐሳቡን ተቀበልኩ:: ዝግጅቱንም ሠራሁት:: አፈ ሊቅ ኅዳር ለምን እንደ ሚታጠን ዘረዘሩ የኅዳር በሽታ መንሥኤን ዘከሩ.... በግን ቦት መጋባትም ክልክል እንዳልሆነ ነውርም እንደሌለበት አስረዱ::... አባትህን ጠይቀው ይነግርሃል የሚለው ቃልም በዚህ መልኩ ተፈጸመ::

አቶ ንጉሤ ከአባታቸው ከአፈሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ጋር ስለነበ ረው ሁኔታ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ:: «ጊዜው በ፲፱፻፶ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው:: በየዓመቱ ጥር ፳፩ የምትውለውን የአስተርእዮ ማርያምን በዓል ለማክበር ቀደም ብለን ተዘጋጅተን ከአባቴ ጋር አገራችን ተጉ ለት እንገባለን:: ላይ ዋሻ ማርያም ከመግባታችን በፊት እግረ መንገዳ ችንን ከአያቶቻችን አገር ከዘንደጉር ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጎራ እንላለን:: ጥር ፲፰ ቀን የሚውለውን የጊዮርጊስን «የስባረአጽሙን» በዓል በዚያ እናከብራለንና «የዘንድሮው እጣነ ሞገር /ቅኔ/ ያንተ ነው» አሉኝ አፈ ሊቅ በጉዞ ላይ እያለን:: አባቴ ባዘዙኝ መሠረት ቅኔውን አዘጋጅቼ ክብር ይእቲውን ከጮህኩ በኋላ እጣነ ሞገሩን የሚመራ ሰው ጠፋ– የሚያዜም:: አፈሊቅ ተመሪ ሆነው ጠጋ አሏ!! እኔ በጆሮ አቸው ቅኔውን ስነግራቸው እሳቸው በዜማ ሲያንቆረቁሩት... አንድ ቦታ ላይ ዜማ ሰበርኩ መሰለኝ «ሽሽሽ» አሉ ቀስ ብለው:: ወዲያው ነገሩ ወደ ሌሎች ካህናት ጆሮ ሳይደርስ የተሰበረውን አስተካከሉትና መሪና ተመሪነቱን ቀጠልን::.... ምልጣኑ ላይ ደግሞ እሳቸው መስቀሉን





ይዘው ይመራሉ እኔ እመራለሁ ይሄ ሁልጊዜ ሳስታውሰው የምኖረው ገጠመኝ ነው:: አባትና ልጅ መሪና ተመሪ ሆነን አሳለፍን::»

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ለዛን ከቁም ነገር ጋር አዋዝተው የመናገር ችሎታም ነበራቸው:: ልጃቸው አቶ ንጉሤ የገጠሙትን እንዲ ህ ያስታውሱታል:: «አንድ ቀን መንገድ ላይ ተገናኘንና ገበሬ «ማኅ በራት» የሚለው ለሴቶች ነው:: ዜና ስታነቡ ብዙ ጊዜ እንደዚያ እያ ላችሁ ትሳሳታላችሁ:: ወይ ደረቁን «ገበሬ ማኅበሮች» በሉት:: ካልሆ ነም «ክቡራትና ክቡራን» እንደሚለው «ማኅበራት-ማኅበራን» በሉት ብለውኝ ከሄዱ በኋላ እንደ ገና ጠሩኝና «ተወው ልጄ! ተወው! ዛሬ ወንዱ ሁሉ ሴት ስለሆነ እንዳሉህ አንብብ» አሉኝና ጉዟቸውን ቀጠሉ::»

አንድ ጊዜ ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ «አራ ዳ ጊዮርጊስን እልቅና ልሹምህ» ይሏቸዋል:: አባታቸው አባ ገብረ ኪ ሮስ እዚያ ያገለግሉ ነበር:: ያን ጊዜ ገዳማትና አድባራት የሚተዳደ ሩት በገጠር ርስት እና በከተማ ቦታ ነበር:: አፈ ሊቅ ደግሞ የመጻሕ ፍተ ሊቃውንት ትርጓሜን በትርፍ ጊዜአቸው ከሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘንድ ይማሩ ነበርና «አባታችን ... አመሰግናለሁ:: ነገር ግን እኔ የቤተ ክርስቲያኑ ርስት ቀረ ብዬ ስሚገት ዋናው እና ትልቁ ቁም ነገር ቃለ እግዚአብሔሩ ይቀራል፤ ትምህርቱም ይረሳል::» ብለው በትኅትና መልሰውላቸዋል::

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ሀገራቸውንና ቤተ ክርስቲያንን ያለ መታከት ሲያገለግሉ ቆይተው ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም ዐርፈዋል:: የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ኅዳር ፲፪ ቀን ፲፰፻፺ ዓ.ም በአደጉበትና በተማሩበት በአዲስ አበባ ጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክር ስቲያን ተፈጽሟል::

*ምንጭ:- የሰባት ዓመት ማስታወሻ ለአፈ ሊቅ አክሊሉ ገ/ኪሮስ /ምሉዕ በኩልሄ/ ከንጉሤ አክሊሉ:: ፲፱፻፹፯*

*- ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ፣*
*ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም*

*- ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ፣*
*ታኅሣሥ ፲፱፻፹ ዓ.ም*